# ዳግም ንባብ በአልወለድም[1]

አንተነህ አወቀ[2]

**አህፅሮተ ጥናት**: *የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው* ***አልወለድም*** *የበርካታ ጥናቶችና የሥነጽሑፍ መድረኮች መወያያ ጉዳይ የነበረና ያለ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን ለየት ባለ መልኩ በልቦለዱ ላይ ትንታኔ ለማድረግ የሞከረ ነው። ትንታኔው የተደረገው ሀዲስ ታሪካዊ ሂስን እንደማዕቀፍ በመጠቀም ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክ ሰነድና ከደራሲው የህይወት ታሪክ ጋር በማዛመድ ነው። በሌላ አገላለጽ የደራሲው፣ የድርሰቱና ድርሰቱ የታተመበት ዘመን ማህበራዊ ፖለቲካዊ አውዶችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። በትንተናውም መሰረት አቤ ጉበኛ የሀገሪቱን ሁኔታ በልቦለዱ ሲገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስን፣ የአክአብና ሎዊ ታሪክን፣ ምሳሌ እንደአደረገ፣ የልቦለዱ መቼት፣ ኢይዝራኤሎስ፣ የአክአብና ኤልዛቤል ግዛት ከሆነው ኢይዝራኤል/እስራኤል እንደተወሰደ፣ የአክአብ መንግስት በኢዩ እንደተወረሰ ሁሉ በልቦለዱም የነሙሴ ገራቢዶስ ፊዩዳላዊ መንግሥት በወታደራዊው መንግሥት በማርሻል ጃፌሮስ እንደተገለበጠ፣ እነዚህ ደግሞ በጥቅሉ የኃይለሥላሴን መንግሥት አስተዳደር እንዳሳዩ እና የወታደራዊውን መፈንቅለ መንግሥት እንደተነበዩ* [3]*፤ አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ አንዳንድ የክርስቶስን ባህሪያት እንደተጋራ መረዳት ተችሏል። ደራሲውም ከአቀንቃኙ ገጸ ባህሪ መምህርነቱን፣ የለውጥ አርአያነቱን፣ መስዋዕትነቱን፣ ከክርስቶስም የእውነት መምህርነቱንና መስዋዕትነቱን ተጋርቶታል ብሎ ማሰብ ይቻላል። ደራሲው በዚህ መልክ ለመጻፍ የቻለው አንድም የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በማወቁ ሲሆን በስልት ረገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ምሳሌ መጻፉ ደግሞ የኃይማኖት ትምህርት እወቀቱን በመጠቀሙ ነው። ከዚህም ደራሲና ድርሰት በዘመኑ ባህል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት እንደሚቀረጹ ሁሉ በተቃራኒው ደራሲውም ሆነ ድርሰቱ ዘመኑን በመቅረጽ ረገድ የሚጫወቱት ሚና መኖሩን መገንዘብ እንችላለን።*

**ቁልፍ ቃላት፡-** *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ፣ ሀዲስ ታሪካዊ፣ በይነ አሀድ፣ በይነ ዲስፕሊን*

---

[1] ይህ ጥናት በ2007 ዓ.ም. በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች ሶስተኛው አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት ላይ ቀርቦ የተሻሻለ ነው።

[2] **አንተነህ አወቀ** በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ነው።
Email: awekeewnetu@gmail.com

[3] *አንዳንድ ተመራማሪዎች (መስፍን፣ ቀን የለውም፤ ግርማይ* (1995)) *ትንበያው አሁን በስልጣን ላይ ያለውንም መንግሥት እንደሚመለከት ይገልጻሉ።*

**የጥናቱ ዳራ**

ይህ ጥናት በደራሲ አቤ ጉበኛ ልቦለድ *አልወለድም* ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው፡፡ አቤ ጉበኛ ከ1925 - 1972 ዓ. ም. የኖረ ሁለገብ ጸሐፊ ሲሆን ልቦለድ፣ ተውኔትና ግጥም ጽፏል፡፡ ደራሲ ብቻ ሳይሆን ሃያሲም ነው፡፡ በደራሲ ሰለሞን ደሬሳ *ልጅነት* የግጥም መድብል እና በዳኛቸው ወርቁ *አደፍርስ* ልቦለድ ላይ ተመስርቶ *‹‹ጎብላንድ አጭበርባሪው ጦጣ››* በሚል ርእስ ሂሳዊ ጽሑፍ አስነብቧል፡፡ ከድርሰቶቹ ውስጥ *ከመቅሰፍት ሠራዊት ይጠንቀቅ ሰውነት* (1949)፣ *የሮም አወዳደቅ* (1953)፣ *የፓትሪስ ሉሙምባ አሳዛኝ አሟሟት* (1954)፣ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው *አልወለድም* (1955)፣ *ምልክአም ሠይፈ ነበልባል* (1956)፣ *የፍጡራን ኑሮ* (1956)፣ *የአመጽ ኑዛዜ* (1956)፣ *ከልታማዋ እህቴ* (1957)፣ *የራሄል እንባ* (1957)፣ *አንድ ለእናቱ* (1961)፣ *የሐሜት ሱሰኞች* (1961)፣ *መስኮት* (1962)፣ *ዕድል ነው በደል?* (1962)፣ *የሕይወት ተርጓሚዎች* (1963)፣ *የረገፉ አበቦች* (1964)፣ *The Savage Girl* (1964)፣ *እሬትና ማር* (1965)፣ *የደካሞች ወጥመድ* (1965)፣ *ፖለቲካና ፖለቲከኞች* (1969) እና *Defiance* (1975) ተጠቃሽ ናቸው፡፡

አቤ መማር የጀመረው በአብነት ትምህርት ቤት ነው፤ በትውልድ አካባቢው ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ለ12 አመታት ከተለያዩ መምህራን ትምህርትን ቀስሟል፡፡ የቅኔ ችሎታውም ላቅ ያለ እንደነበርና ቅኔ አዘራረፋቸውን ሰምቶ ያቃናላቸው መምህሩ በችሎታው ተደንቀው እሱ አቤ ጉበኛ ሳይሆን አቤ ጉደኛ ነው ማለታቸው ተጽፏል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት እስከ ስድስተኛ ክፍል ጎጃም ዳንግላ የተማረ ሲሆን ወደ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ በመሪጌታነት በሃና ማሪያም አገልግሏል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱንም አጠናቋል፡፡ አቤ የተፈጥሮ ማስተዋሉ በአብነትና በዘመናዊ ትምህርት በመታገዙ የድርሰት መንፈሱን አንቀቶለታል፡፡ በስራው አለም በጋዜጠኝነት ሙያ መስራቱም ከተፈጥሮ ድፍረቱ ጋር ተደማምሮ ታዋቂ ደራሲ ለመባል አብቅቶቷል፡፡ አቤ በጋዜጣ ላይ መጻፍ መጀመሩ የመንፈስ ብርታት ሆኖት ከላይ የተጠቀሱትን ድርሰቶች ለመጻፍ በቅቷል (ኤልያስ፣ 1991፣ Molvaer፣ 1997)፡፡

ብዙዎቹ የአቤ ድርሰቶች ፖለቲካ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ *የሮም አወዳደቅ፣ አልወለድምም ሆነ ምልክአም ሰይፈ ነበልባል* አስከስሰውታል፤ መልስ እንዲሰጥም አስገድደውታል፡፡ በተለይም በ*አልወለድም* ድርሰቱ ግዞት ወርዶበታል፡፡ መጽሐፉም በሁለት *ሥርዓቶች* (በኃይለ ስላሴና በደርግ) ታግዷል፡፡ ከግዞት በኋላ ሙሉ ትኩረቱን በድርሰት ላይ አድርጎ በሚያገኘው ገቢ ለመተዳደር ሞክሮ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ምናልባትም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የሙሉ ጊዜ ጸሐፊ (professional writer) ለመባል የበቃ ነው፡፡ በ1965 የኢንተርናሽናል ራይቲንግ ፌሎውሽፕ ፕሮግራም ለመካፈል ወደ አሜሪካ አይዋ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ሄዶ ነበር፡፡ ሆኖም ጥቂት እንደከረመ በሀገር ቤት አብዮት በመቀጣጠሉና የመንግሥት ለውጥ በመደረጉ ተመለሰ፤ ሁኔታውን በገዛ ብዕሩ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡-

> በአገራችን ላይ የለውጥ እንቅስቃሴ መጀመሩን ሰማሁ፡፡ ከሰማኋቸው ወሬዎች በተረዳሁት መሠረት ሁኔታው መልክና አቅጣጫ የሌለው ወደ ደም መፋሰስ የቀረበ ሆኖ ታየኝ፡፡ ወደ አገሬና ወደ ቤተሰቤ ተመልሼ ሞቱንም ሽረቱንም ከአገሬ ሕዝብ ጋር ከመካፈል የበለጠ ተገቢ ዕድል እንደሌለኝ በማመን ወደ አገሬ የምመለስበትን ቀን ለማፋጠን ወሰንሁ፡፡ የጥናቱን ባይሆንም ከጉብኝት ጊዜዬ ቀሪውን አቋርጬ ወደ አገሬ ተመለስሁ (ግንቦት 9/1966 አዲስ ዘመን ጋዜጣ በኤልያስ (1991፣ገጽ 40) እንደተጠቀሰው)፡፡

አቤ ወደሀገሩ ከተመለሰ በሁዋላ የለውጡ አራማጆችና ተቀናቃኞቻቸው ይከተሉት በነበረው መስመር ደስተኛ አልነበረም፡፡ ይህን አቋሙንም በተለያዩ ጊዜያት በጋዜጣ ላይ በመጻፍ ያሳውቅ ነበር፡፡ በተለይም ደርግ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ ሁኔታው ስላልተመቸው *ፖለቲካና ፖለቲከኞች* የሚል ቲያትር ጽፎ ለተመልካች በሀገር ፍቅር ቲያትር መድረክ ቀርቦ ታይቷል፡፡ ይህን ቲያትር አስመልክቶ የሚከተለውን ብሏል፡-

> ይህ ቲያትር የተጻፈው የምንም ዓይነት ፍልስፍና ማስፋፊያ ወይም መቃወሚያ እንዲሆን አይደለም፡፡ ዋና አላማው የአገራችን ለውጥ ተጀምሮ እየገፋ በመጣበት አንድ ጊዜ ላይ የታየውንና አሁንም ባንዳንድ ሰዎች ላይ የሚታየውን ቅሌትና አሳሳችነት ለሕዝብ ገልጾ ለማሳየትና ፍርዱን ለባለ ጉዳዩ ሕዝብ ለመተው ነው፡፡ … ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ ከግል ትችት አልፈው በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ ወረቀት በመበተን ለማሳጣት ሞክረዋል፡፡ ሰሚ ቢያጡ እንጂ "ፀረ ሶሻሊስት፣ ፀረ አብዮት፣ አድሃሪ" ሲሉኝ ምን እንዲደረግብኝ መፈለጋቸው ኑሯል?
>
> በነሱ ቤት አንድ ሰው ምንም ያህል ለሀገሩ ጠቃሚ ይሁን፣ ምንም ያህል ወገኖቹን ይውደድ በእነርሱ አስተሳሳብ ካልተስማማ መኖር የማይገባው ሰው ነው፡፡ … አንዳንድ ሳዲስቶች (በሰው ስቃይ የሚደሰቱ ጉዶች) እንደሚመኙት ከወገኖቼ በአንዱ እጅ ብሞት እንኳ በዚያ ዕብድ ጭካኔ የብዙዎች ወገኖቼን ቅን መንፈስ ለውጬ አላየውም፡፡ ያለኝን ያህል ችሎታና ዐቅም ካስፈለገም ሕይወቴን ጭምር ለሀገሬ ከማበርከት ከቶውንም ወደኋላ አያሰኘኝም፡፡ … አሁን ችግር የሆነብን በአገራችን ሁኔታዎች ላይ የምንመለከታቸውን ችግሮች እንዳንወያይባቸው ለምን ትንፍሽ ብላችሁ ማለታቸው ነው፡፡ ለመሆኑ እነግርማዊ ጭጭ ይበሉና እነ አፈ-ንጉሥ አይተንፍሱ እንደሚመኙት ሁሉ ሥልጣን የነሱ ቢሆን ኖሮ ምን ሊሠሩ ኑሯል? ለነጻነት ለዕኩልነትና ፍትህ ስንታገል ኖርን የሚሉ ሰዎች ለምን ሀሳብን በመጨቆን ያምናሉ? ጥቅምን ሲያሳድድ ሊደርስ የሚችለውን የማይጠገን አደጋ እያዩስ እነሱም ለምን ይታወራሉ? እኔ ግን ማንም ዋሾ ይጥላኝ እንጂ ያየሁትን መግለጼን መተውን እንደከፍተኛ ሀገርን መካድ ስለምቆጥረው ያየሁትን እውነት በቀልድ መልክ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ (አቤ በኤልያስ፣ 1991፤ ገጽ 50 እንደተጠቀሰው)

አቤ ጉበኛ *በምልክዓም ሰይፈ ነበልባልም* ሆነ በሌሎች ድርሰቶቹ በገኘው መደብ አባላት ትችትና መንገላታት የደረሰበት ቢሆንም በተለይ በ*አልወለድም* በንጉሡ ዘመን በደል ደርሶበታል፡፡ ድርሰቱ ከገበያ እንዲወጣና ከስርጭት እንዲታገድ ተደርጓል፡፡ ሲያነብ የተገኘ ሳይቀር ይቀጣ ነበር፡፡ በስደት ኢሊባቡር ክፍለሀገር፣ ሞቻ የተባለ የገጠር ስፍራ ከሰዎች ተገልሎ እንዲኖር ተግዟል፡፡ በግዞት በነበረበት ወቅት ከወጣቶችና ከውጭ ሀገር ዜጎች እንዳይገናኝ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር፡፡ አቤ መንግሥትን ተችቶ መጻፍ ቢያቆም ኖሮ ግን ይህ ሁሉ እንግልት ባልደረሰበት ነበር፡፡ ንጉሡ መንግሥትን እየተቸ መጻፍ ቢያቆም የደብረብርሃን አስተዳዳሪ ሊያደርጉት ቃል ገብተውለት ነበር፡፡ ሆኖም ከግል ምቾቱ ይልቅ የህዝብ ጠበቃነቱን ምርጫው አድርጎ መንገላታትን መርጧል (ኤልያስ፣1991፤ Molvaer, 1997)፡፡

በደርግ ሥርዓትም ከዚህ አቋሙ የተነሳ በየጊዜው በጋዜጣ በሚጽፋቸው ጽሑፎቹና በሚከተለው የፖለቲካ አቋሙ እንዲሁም በፖለቲካና ፖለቲከኞች ተውኔቱ ጥርስ ውስጥ ስለገባ ወደ ትውልድ ስፍራው ቢሰደድ እንኳ ብዙዎች የደርግ እጅ አለበት ብለው በሚጠረጥሩት ግድያ በ1972 ህይወቱ አልፏል፡፡ ደርግ *አልወለድምን* ለፖለቲካ ፍጆታ እንዲታተም ቢፈቅድም ጉዳዩ እሱንም ይነካ ስለነበር ለሁለተኛ ጊዜ ከገበያ እንዲወጣ አድርጓል (ኤልያስ፣ 1991)፡፡

**የጥናቱ መነሻ ሀሳብ**

ልቦለዱ በተናጠልም ሆነ ከሌሎች ጋር እየተጣመረ በስፋት ተጠንቷል፡፡ ፍቅሬ (1982) በፒ.ኤች. ዲ ቴሲሱ የ15 ደራሲያንን ልቦለዶች ያጠና ሲሆን የአቤ ጉበኛ *አልወለድም* ከነዚህ ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ፍቅሬ (ገጽ 173 - 182) ልቦለዱ ምንም እንኳ በታተመበት ዘመን የነበረውን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያንጸባረቀ ቢሆንም በጥቅሉ ሲታይ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ዘረያዕቆብ ፍልስፍና ላይ እንደተመሰረተና ከሴራው አንጻር የፋንታስቲክ ሥነጽሁፍ ተጽእኖ እንደሚታይበት ይገልጻል፡፡ ፍቅሬ እንደሚለው ልቦለዱ ፋንታሲ የሚታይበት ቢሆንም ልቦለዱ የዘረያዕቆብን ፍልስፍና (ቴሲስ) መሰረት አድርጎ የተነሳ ነው ሲል የሰጠው መግለጫ ግን የተጋነነ ነው፡፡ ዘረያዕቆብ ስለእውነተኛው ሃይማኖት ያነሳው ጉዳይ በ*አልወለድም* የተነሳ ቢሆንም የልቦለዱ ዋነኛም፣ ብቸኛም መሰረት አይደለም፡፡ ሃይማኖቱ የፖለቲካው መሳሪያ ሆኖ ቢያገለግልም በዋነኛነት የተወሳው ከልቦለዱ አቀንቃኝ ገጸ ባህሪ ጥምቀት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በእርግጥ በታሪኩ ፍሰት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሃይማኖት ተቋማት የመንግሥት አገልጋይ በመሆናቸው ይተቻሉ፡፡

እንደ ፍቅሬ ሁሉ ሌሎችም አጥኚዎች ለምሳሌ Kane (1975፣ ገጽ 191 — 195) በጉዞ ላይ ከተመሰረቱ ግብረ-ገባዊ ሥነጽሑፎች (journey type of moralistic literature) መመሳሰሉን ይገልጻል፡፡ ሆኖም *አልወለድም* ከስነምግባራዊነቱ ይልቅ ፖለቲካዊነቱ ነው ገዝፎ የሚታየው (በእርግጥ Kane

መግለጽ የፈለገው ፖለቲካዊ ስነምግባርን ካልሆነ በስተቀር) ፡፡ የአልወለድምን ፖለቲካዊ ልቦለድነት በተጨባጭ ካስነበቡ ጥናቶች መካከል የግርማይ (1995) "Literature and Politics in Ethiopia: A Case Study of Abe Gubenya's Alwellwdim" ዋነኛው ነው፡፡ ግርማይ በዚህ ጥናት ልቦለዱ የኃይለሥላሴን ሥርዓት ፖለቲካዊ አገዛዝ መግለጹንና የደርግን አገዛዝ በተጨባጭ መተንበዩን ልቦለዱን ከተለያዩ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ሰነዶች ጋር እያገናዘበ ይገልጻል፡፡ በልቦለዱ ከመፈንቅለ መንግሥቱ በፊት ያለውን ታሪክ ከኃይለሥላሴ መንግሥት ማህበረ ፖለቲካ ሁኔታ ጋር ሲያገናዝበው ከመፈንቅለ መንግሥቱ ጀምሮ ያለውን ሂደት በተለይም ከመሬት፣ ከዲሞክራሲ፣ ከሚዲያና ‹ሴንሰር› ጋር በተያያዘ ከወታደራዊው ደርግ ተጨባጭ ማህበረ ፖለቲካዊ እውነታ ጋር ያገናዝበዋል፡፡ ተስፋዬ (1986) "The Portrayal of Society and the Concept of Modernization in Abbe Gobegna's Novels" በሚለው የማስተርስ ዲግሪ ጥናቱ በልቦለዱ በንጉሡ ዘመን የነበሩ ማህበረ ፖለቲካዊ እውነቶች እንዴት እንደተንጸባረቁ ይገልጻል፡፡ መስፍን (ቀን የሌለው) ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ የተገለጹትን ትእምርቶችና ተምሳሌቶች ውክልና ላይ በማተኮር በልቦለዱ የተገለጹት ማህበረ ፖለቲካዊ እውነቶች በእማሬው የምንረዳቸው ሳይሆኑ በወቅቱ የነበረውን እውነታ በተምሳሌት የገለጹ ናቸው ሲል ተምሳሌቱን ለመፍታት ሙከራ ያደርጋል፤ እንደ ግርማይ ሁሉ መስፍን ልቦለዱ የደርግን አገዛዝ አስቀድሞ ተንብዩዋል ሲል ያስረዳል፡፡ ትንበያው የደርግን ብቻ ሳይሆን ይህንንም መንግሥት እንደሚመለከት ጠቆም አድርጎ ያልፋል፡፡ ሆኖም የመስፍን ጥናት ጠቃሚ መረጃዎችን የሰጠ ቢሆንም የምርምርን መንገድ የተከተለ ነው ማለት ያስቸግራል፡፡

ይህ ጥናት ከዚህ ቀደም በተሠሩት ጥናቶች አልተስተዋሉም ብሎ አጥኚው ባመነባቸው አንዳንድ ጉዳዮች ላይ አዲስ ትንታኔ ለመስጠት ይሞክራል፡፡ አዲስ ዕይታም ይፈጥራል፡፡ መስፍን የልበለዱ መቼት በተምሳሌት ኢትዮጵያን የገለጸ ነው ሲል እንዴት የሚለውን ግን በማስረጃ ተንትኖ አያሳይም፡፡ ይህ ጥናት ይህን ክፍተት ለመሙላት ይሞክራል፡፡ ልቦለዱንም ለመረዳት ከግርማይ በተለየ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስን (New Historicism) ማዕቀፍ አድርጎ ይተነትናል፡፡ መስፍን የተጠቀመው ምንም አይነት ንድፈ ሃሳባዊ ማእቀፍ የለም፡፡ በዚህ ጥናት ትንተናው ይበልጥ የሚያርፈው የልቦዱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ በመፍታት ነው፡፡ ሀዲሰ ታሪካዊ ሂስ የተመረጠው በይነ ንባብ (interdisciplinarity) ስለሚፈቅድና ድርሰቱን ከደራሲውና ድርሰቱ ከተጻፈበትና ከሚነበብበት ማህበረ ፖለቲካ ዐውድ ጋር ማገናዘብ ስለሚያስችል ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ የደራሲ አቤ ጉበኛ ረዥም ልቦለድ የሆነው አልወለድምን በሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ንድፈ ሃሳብ ማእቀፍነት በመተንተን አዲስ ዕይታ መፍጠር ነው፡፡ ጥናቱ የአቤ ጉበኛን ልቦለዶች ልንረዳባቸው የምንችልባቸውን አማራጮች ያሳያል፤ በሥነጽሑፍ ስራዎች ላይ የሚደረግ ምርምርን ያግዛል፡፡ አማራጭ የመወያያ ጉዳይም ይሆናል፡፡

## የጥናቱ ስልት

የጥናቱ ስልት ገላጭ ሲሆን ከላይ እንደተጠቀሰው ሀዲስ ታሪካዊ የተባለውን ሂሳዊ ንድፈ ሃሳብ በመጠቀም በልቦለዱ ላይ ጥልቅ ንባብና ትንተና ያደርጋል። ሀዲሰ ታሪካዊ ሂስ ልቦለዱን ከድርሰቱ (textual context)፣ ከደራሲውና (authorial context) ድርሰቱ ከተጻፈበት ዐውድ (contextual context) ጋር በማገናዘብ መረዳት ያስችላል። እንዲሁም አንድን ድርሰት ከሌሎች ድርሰቶችና ዲስኩሮች በማገናዘብ የሚደረግ ትንተናን ይፈቅዳል። የሥነጽሑፍን ድርሰት በጥልቀት ለመረዳት የታሪክ፣ የፖለቲካና የግለታሪክ መጽሐፎችን ማንበብ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ሁሉ ታሪክንና ፖለቲካን ይበልጥ ለመረዳትም በዘመኑ የተጻፉ ሥነጽሑፎች ከፍተኛ ሚና አላቸው የሚል መርህ አለው (Bertens፣ 2001፣ ገጽ 180; Doğan፣ 2005፣ ገጽ 80)። በአጭሩ ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ ሥነጽሑፍ በይነ ዲሲፒሊናዊ ነው ብሎ ስለሚያምን በይነ አሀዳዊ (intertextuality) ንባብ ይፈልጋል የሚል አቋም ያራምዳል (Holub፣ 1992፣ ገጽ 174; Zekiye፣ (?)፣ ገጽ 62)። ሀዲስ ታሪካዊ ሂስ የትኛውም ድርሰት በታተመበት ባህላዊና ፖለቲካዊ አሰራር እንደሚቀረጽ ሁሉ በተራው ዘመንን የመቅረጽ ኃይል አለው ብሎ ያምናል። የትኛውም ሥነጽሑፍ ከርዕዮተ ዓለም ነጻ ነው ብሎ አያምንም። ድርሰት ከፖለቲካ ነጻ ነው ብሎም አያስብም። ድርሰት ማህበረሰብን የመቅረጽ ሚናም እንደሚጫወት ይገልጻል። የሚከተለው የBertens (2001፣ ገጽ 177) ሃሳብ የስነጽሑፍን ፖለቲካዊነት በሚገባ ይገልጻል፡-

> The literary text is a time-and place-bound verbal construction that is always, in one way or another political; because it is inevitably involved with a discourse or an ideology, it cannot help being a vehicle for power.

በዚሁ መሰረት በሚቀጥለው ክፍል ልቦለዱን ከደራሲው፣ ከዘመኑና ከድርሰቱ ዐውድ ጋር በማገናዘብ፣ በተጨማሪም ከመጽሐፍ ቅዱስና ከታሪክ መጻሕፍት ከህይወት ታሪክና ከሌሎች ሰነዶች ጋር በማዛመድ ትንተናው ይደረጋል።

## ሥነጽሑፋዊ ውክልና በ*አልወለድም*

አቤ ጉበኛ በ*አልወለድም* የመጀመሪያ ዕትም ልቦለዱ ጨርሶ ፈጠራ እንደሆነና የማናቸውንም ሀገራት ፖለቲካ እንደማይመለከት ገልጾ ነበር፤ ይህንንም ማሳካት እንዲያስችለው ፈጠራ መቼትና ፈጠራ ገጸ ባህሪያትን ተጠቅሟል። መቼቱን በሀገረ ኢይዝራኤሎስ እና በዋናዋ ከተማ አቃንያ ሲያደርግ ገጸ ባህሪያቱንም ስም የለሽ አድርጎ ስሏቸዋል። በስም የተጠቀሱት ሀገርና ከተማም በኢትዮጵያ የተለመዱ አይደሉም። የገጸ ባህሪያቱንም አሳሳል አስመልክቶ አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ በግብር እንጂ በስም አልተገለጸም። ሌሎችም አጃቢ ገጸ ባህሪያት ለምሳሌ የአቀንቃኙ ገጸ ባህሪ እናትና አዋላጁ ሀኪም በስማቸው አልተገለጹም። ስማቸው የተገለጸው በኢይዝራኤል የቀድሞ ሥርዓት ገዥ

ከነበሩት ውስጥ አንዱ የመሬት ከበርቴ የነበረው ሙሴ ገራቢዶስና መፈንቅለ መንግሥት አድራጊው ማርሻል ጳፌሮስ ናቸው፡፡ የእነዚህም ሰዎች ስሞች ቢሆኑ ለኢትዮጵያውያን አዲሶች ናቸው፤ አልተለመዱም፡፡

አቤ ይህን ማድረጉ ከሴንሰር ክፍል የሚመጣውን ችግር ለማለፍ እንጂ በልቦለዱ የተገለጸው ህይወት የሌሎች ህዝቦች ሆኖ አይደለም፡፡ የኢትጵያውያን ነው፡፡ የኢትዮጵያውያንም በመሆኑ ልቦለዱ ከስርጭት ታግዷል፤ ከገበያና ከቤተመጽሐፎች ተሰብስቧል፡፡ ከአንባቢያን እጅ ተለቅሟል፡፡ ደራሲውም ግዞት ወርዷል፡፡ ሲያነብ የተገኘም ሰው ተጠያቂ ሆኗል፡፡ አቤም ቢሆን ከ1966 አብዮት በሁዋላ ለሁለተኛ ጊዜ በታተመው በልቦለዱ አዲስ መግቢያ "አልወለድምን በጻፍሁ ጊዜ አገሬ በጨለማ የግዜው ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በጨለማ የወደፊት እድል ላይ ትታየኝ ነበር" (1993፣ ገጽ 20) ሲል ለመጻፍ ያነሳሳውን ምክንያትና በልቦለዱ የተገለጸው እውነታ የሀገሩ ሁኔታ እንደሆነ ገልጿል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በልቦለዱ ውስጥ የተነሳው ማህበረ-ፖሊቲካ እውነት የኢትዮጵያ ሲሆን በተለይም የኃይለሥላሴ ሥርዓት ነው፡፡ ይህም ከአቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ንግግርና በልቦለዱ ከተጠቀሱት ፖለቲካዊና ታሪካዊ እውነቶች መረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አቀንቃኙ ስለልቦለዱ መቼት ስለ ኢይዝራኤሎስ ሲገልጽ እንደሚከተለው ነበር፡-

> ሥርዓቱን ማን እንዳቃወሰው አላውቅም፡፡ እግዚአብሄር ይሁን ሰው ወይም የተፈጥሮ ጣጣ ማን እንዳበላሸው አልተረዳሁትም፡፡ ግን ሥርዓቱና ለኛ ተገቢ የሚመስለን ነገር ሁሉ በተመሰቃቀለበት ዓለም ሰዎች ሁሉ ይኖራሉ፡፡
>
> እኔ የተወለድሁባት ኢይዝራኤሎስ የተባለቺው ደሴት በወራሪዎች ስትበዘበዝና ስትጠቃ ስትገዛም ኑራ ነጻነቷን ካገኘች በኋላ ራሷ የተበላሸች አገር ነበረች (*አልወለድም*፣ ገጽ 37)፡፡

እንደኢይዝራኤሎስ ሁሉ ኢትዮጵያም ሙሉ በሙሉ ቅኝ አትገዛ እንጂ ጣሊያን ለአምስት አመታት ነጻነቷን ተፈታትኗት ነበር፤ ነጻነቷን ካስከበረች በኋላም ህዝቡ ሀገሪቱ የተሻለ ዕድል ይገጥማታል ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር፡፡ ንጉሡም ቢሆን የተሻለች ኢትዮጵያን ለመመስረት ቃል ገብተው ነበር (በሪሁን፣1992)፡፡ ይህ ተስፋ ግን እውን አልሆነም፤ ከጊዜ ወደጊዜ አገዛዙ እየከፋ ሀገሪቱ ወደ ውድቀት እያመራች ትሄድ ነበር፡፡ መሳፍንቱና መኳንንቱ ሀብት (በተለይም መሬት) እያግበሰበሱ ገበሬውን ከእርስቱ እያፈናቀሉ ባዶውን ያስቀሩትና ለስደት፣ ለጭሰኝነት ይዳርጉት ነበር፡፡ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እየተገፈፉ ህዝቡ ይማረር ነበር (ባህሩ፣ 2002)፡፡ ይህ ሁኔታ ነው አቤን አልወለድምን እንዲጽፍ ያነሳሳው፡፡ በቤተክርስቲያንና በመንግሥት ፖለቲካ መካከል ያለው ቁርኝት፣ በጭሰኛውና በባለእርስቱ፣ በአሠሪውና ሠራተኛው፣

ሀብት ባለውና በሌለው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ያለው ችግር ነው እንዲጽፍ ያነሳሳው፡፡

በ*አልወለድም* የተወከለው የንጉሡ ሥርዓት ብቻ አይደለም፡፡ የልቦለዱ የመጀመሪያው ክፍል የንጉሡን ሥርዓት የሚገልጽ ሲሆን ከመፈንቅለ መንግሥቱ ቀጥሎ ያለው ክፍል ደግሞ ደራሲው የሀገሪቱን መጻኢ ዕድል የተነበየበትና ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት አይቀሬ መሆኑን ያሳየበት ነው፡፡ በግርማይ (1995) እንደተጠቀሰውና አንባቢ ከንባቡ ማስተዋል እንደሚችለው ኢይዝራኤሎስ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በንጉሣዊ አገዛዝ የምትተዳር ሀገር ናት፡፡ የመደብ ስብጥሯም ነገሥታትና መሳፍንት፣ ፊዩዳሎችና ከበርቴዎች የገዥው መደብ አባላት ሲሆኑ የቢሮ ሠራተኛው፣ ምሁሩ፣ ወታደራዊ ሹማምንቱ ደግሞ የመካከለኛው መደብ አባላት ናቸው፡፡ ወዝአደሩ፣ ጭሰኛው ገበሬው፣ ጎዳና ተዳዳሪው፣ ሴተኛ አዳሪዎችና የኔቢጤዎቹ ደግሞ የዝቅተኛው መደብ አባላት ናቸው፡፡ ዋነኛ የምርት ግንኙነቱም በአንድ በኩል በገዥዎቹ በነገሥታቱ፣በመሳፍንቱና በባላባቶቹ በሌላ በኩል በተገዥው ጭሰኛ ገበሬና ሰራተኛ መካከል ያለ ነው፡፡

እንደኢይዝራኤሎስ በኢትዮጵያም በመንግሥትና ሃይማኖት በኩል ያለው ግንኙነት ጥብቅ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የመንግሥት መሳሪያ ሆና ታገለግል ነበር፡፡ ካላቸው ጥብቅ ግንኙኙነት የተነሳ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመሬት ባለቤት የነበረች ስትሆን የመሬት ይዞታን የሚያሻሽሉ አዋጆች እንኳን የቤተክርስቲያኒቱን መሬት ጉዳይ አይመለከቱም ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ባህሩ (2002፣ ገጽ 193) "the church was exempted from the abolition order" ሲል በ1940 የታወጀው የመሬት ማሻሻያ አዋጅ እንኳ ቤተክርስቲያኒቷን እንዳልተመለከታት ገልጾ ነበር፡፡ ይህ በኢይዝራኤሎስና ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ጨቋኝ ስርዓቶች ባሉበት ሁሉ የተለመደ መሆኑን ቀጥሎ በTyson (2006፣ ገጽ 285) ከተጠቀሰው ሃሳብ መረዳት እንችላለን፡-

> even the dictator of a small country doesn't wield absolute power on his own. To maintain dominance, his power must circulate in numerous discourses, for example, in the discourse of religion (which can promote belief in the "divine right" of kings or in God's love of hierarchical society).

እንዲህ በመሆኑም ነው በ*አልወለድም* ውስጥ በኢይዝራኤሎስ መንግሥት አመጸኛ ተብሎ የሞት ፍርድ ለተፈረደበት አቀንቃኝ ገጸ ባህሪ አስከሬን ማረፊያ ቦታ ለመስጠት የእምነት ተቋማቱ ፈቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩት፡፡ ምክንያቱ ደግሞ መንግሥት ላይ ማመጹ ነው፡፡

በፕሬስም ጉዳይ ኢይዝራኤሎስና ኢትዮጵያ አንድ ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት አልነበረም፡፡ ሚዲያው የመንግሥት አፍ ብቻ ነበር፡፡ ጸሐፍት መንግሥትን ማወደስ እንጂ መተቸት አይችሉም ነበር፡፡ አቤ በልቦለዱ መግቢያ

ከመጽሐፉ ጋር በተያያዘ የገለጸውም ማብራሪያ በወቅቱ ለነበረው ሁኔታ አስረጂ ነው፡፡

> ይህ መጽሐፍ የዛሬ 11 ዓመት ገደማ በደንቡ ምርመራ አልፎ ታትሞ በወጣ ጊዜ ታላቅ ችግር ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ከአንድ ዓመት በላይ ሲያጨቃጭቀኝና በየቦታው ሲያስጎትተኝ ቆይቶ በመጨረሻው በእሳት ነዶ የሰማዕትነት ጽዋውን እስከተቀበለበት ቀን ድረስ ብዙ የክርክር መልሶች እንድጽፍለት አስገድዶኛል፤ በፖሊስ አሳስሮኛል፡፡ ብዙ ጠላቶችም አፍርቶልኛል፡፡

እንደግርማይ (1995) በልቦለዱ የተወከለው የኃይለሥላሴ ሥርዓት ብቻ አልነበረም፡፡ የደርግም ነው፡፡ በመፈንቅለ መንግሥት ስልጣን የተቆናጠጠው የነማርሻል ጃፌሮስ መንግስት የደርግን ሥርዓት ይወክላል፡፡ እነማርሻል ጃፌሮስ እንደ ደርግ መንግሥት ሁሉ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናትን በሞት ፍርድ ቀጥተዋል፡፡ የሀገሪቱን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በወታደራዊ ባለስልጣናት አስይዘዋል[4]፡፡ የህዝቡ የመናገር መብት ተገድቧል፡፡ የፕሬስ ነጻነት አልነበረም፡፡ ይህን የኢይዝራኤሎስ ፕሬስ ችግር ሁኔታ ቀጥሎ ከቀረበው ከአቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ትረካ መገንዘብ ይቻላል:-

> የግል ጋዜጦች ሁሉ በወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን ሥር ከመዋላቸው አንዳንዶቹም ከመዘጋታቸው በላይ ስለህዝቡ ኑሮ ጥቂት ማጉረምረም የሚያሳዩ የፖለቲካ ሰዎች ሁሉ እየተያዙ ያለፍርድ ይታሰሩ ጀመር፤ አንድ ሰው በጽሑፍም ሆነ በንግግር ወታደራዊውን መንግሥት ከማመስገንና የድሮዎቹን መሪዎችና ሀብታሞች ከመንቀፍ ያለፈ ሃሳብ የመግለጽ መብት አጣ፡፡ … ማንም ሰው ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ አድርጎ የመቃወሚያ ቀርቶ የአቤቱታ ድምጽ እንዲያሰማ የማይፈቀድለት ሆነ (አልወለድም፣ገጽ 144)

አቤ ጉበኛን ነቢይ ጸሀፊ ያሰኘው አንዱ ምክንያትም ይህንና ይህን የመሳሰሉትን የመፈንቅለ መንግሥቱንና በሥርዓቱ ውስጥ የሚታዩትን የፕሬስና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በልቦለዱ መግለጹና እውነታው ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር መመሳሰሉ ነው፡፡ በደርግ ሥርዓት ፕሬሱ የመንግሥትን አቋም ከማንጸባረቅ ውጭ ትችቶችን አያስተናግድም ነበር፡፡ ግርማይ በአልወለድም በኢይዝራኤሎስ የተገለጸውን የፕሬስ ነጻነት ችግር ከወታደራዊው የደርግ መንግሥት ጋር እያነጻጸረ ሲተነተን የደርግን ሁኔታ የገለጸው በሚከተለው መልኩ ነበር ፡- "*Like all military dictatorships, it saw the presence of an independent press inimical to its existence.*" (ግርማይ፣ 1995፣ ገጽ 151)፡፡ በማስረጃነት በግርማይ የተጠቀሰው አለም (1978) የደርግን ፕሬስ ሁኔታ የገለጸው እንዲህ በሚል ነበር:-

---

[4] አቤ ብቻ ሳይሆን ሀዲስ አለማየሁም ቢሆኑ በ*ፍቅር እስከ መቃብር* (1958) ሥርዐቱን በካብ መስለው የታችኛው ሲያፈነግጥ የላይኛው መናዱ የማይቀር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

> The military coup of September 1974 brought its own brand of mind control, and the flicker of hope ignited by the February Revolution was extinguished. Although the former censors remained in their posts, the military junta assigned a captain and a major to oversee the work of the press, radio and television.
>
> Since the 'revolution' every song, old or new, has been censored. Some are played with verses deleted, some have been shelved permanently. (ግርማይ፣ 1995፣ ገጽ 151)

አቤን ነቢይ ያሰኘው ሌላው ጉዳይ የኃይለሥላሴን መንግሥት መግለጹ ብቻ ሳይሆን ከላይ በጥቅሱ እንደተገለጸው ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥቱን መተንበዩ ነበር። እንደኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሁሉ በልቦለዱ ሂደት በኢይዝራኤሎስ ለውጡን ህዝቡ የተቀበለው በደስታ ነበር፤ ምክንያቱ ደግሞ የተሻለ አገዛዝ ተስፋ ማድረጉ ነው። ይህ ሁኔታ በልቦለዱ ውስጥ የተገለጸው በሚከተለው መልኩ ነበር፦

> አዲስ ወታደራዊ መንግሥት በሚሰብክበት ጊዜ ህዝቡ በየቦታው ተስፋውን እየተመገበ ይፈነጭ ነበር። በየጊዜው ወደከተማ ስመላለስ እንዳየሁት ሕዝቡ አዲሱን መንግሥት ያላንዳች መቃወም ተቀብሎት ነበር። የባላገሩ ፏሪም ምንም አልተቀንቀሳቀሰም ነበር። ነገር ግን ከጊዜ በኋላ አንድ ሁለት ዓመት ቆይቶ በገበሬው በነጋዴው በባለ ኢንዱስትሪውና በሌላውም ሠርቶ ፏሪ ህዝብ ላይ ግብርና ቀረጥ እየተደራረበ ለጦር አለቆች መቀማጠያ ለጦር መሣሪያዎች ማደርጃና ማብዣ ሆነ።
>
> የሕዝቡም ጠቅላላ ኑሮ ሰላም ከማጣቱና መንሰራፊያ ከመሆኑ በቀር ከድሮው በምንም አልተሻለ። …
>
> ለሥልጣንና ለሹመት የሚመረጡት የጦር መኮንኖች ብቻ ስለሆኑ ስንቱ አዋቂ በንግድና በእርሻ ሥራ ራሱን ለመርዳት ካልሆነ በቀር በመንግሥቱ ድርጅቶች ገብቶ የሥራ ተካፋይ ለመሆን ዕድል አጣ (*አልወለድም*፣ ገጽ 143 — 144)

ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ወታደራዊ መንግሥቱ አመጣሁት ብሎ ስለሚመጻደቅበት ለውጥ ሲገልጽ እንደሚከተለው ነበር፦

> የኛዎቹ አዲስ መንግሥት መሥራቾችም በኃይል ጭጭ አድርገው እየገዙን እያየን ‹አገራችንን ከጭቆና አገዛዝ ወደ ነጻነት መራናት› እያሉ ይፎክሩብናል። ይኸውም የጊዜውን ነፋስ በመከተል ነው።…ለውጡ የትኛው ነው? እናንተ ለውጥ ብላችሁ የምታምኑት የጥቂት ሀብታሞችን መሞትና መንገላታት ነው? እኛ የምንፈልገው እንዳይጎዱንና እንዳያጠቁን እንጂ እነሱ ቢሞቱ ደማቸውን አንጠጣው፤

> ቢሰቃዩና ቢንገላቱ የመንፈስም ሆነ የአካል ደስታ አናገኝበት! ወይስ መሻሻል የምትሉት ሲቪል ሹም ሽሮ ወታደራዊ ሹም መሾሙን ነው? ወይስ ከሕዝብ አንዱ ድምጽ ሊሰጥበት የማይችለውን ለስሙ ግን የህዝብ መንግሥት (ሬፑብሊክ) የሚባል መንግሥት መቋቋሙን ነው? ኧረ ለውጥ የምትሉት የቱን ነው? ድርብ ቀረጥና ግብር መክፈሉን ነው? ጠቃሚ ድርጅቶችን እያደከሙ ለውጭ ጠላት እንኳ ሳይሆን ያገርን ሕዝብ ለማጥቃት የጦር ድርጅቶችን ማስፋፋቱን ነው? እንግዲህ አዲሱ መንግሥት ያሳየን ለውጥ ይህን ነው፤ ይህን ከሆነ መሻሻል የምትሉት ሌላ ነገር ነው። (*አልወለድም*፣ 150 -151)

በኢትዮጵያም የነበረው ሀቅ ይህ ነው፤ ሲቪል ተሽሮ ወታደር ነው የተሾመው። 60 የሚሆኑ የቀድሞ ሥርዓት መሪዎችና ቤተሰቦች ናቸው የተረሸኑት። ያስፋፉት ህዝቡን ሰጥ አድርጎ ለመግዛት የሚያስችላቸውን የጦር ሃይል ነው። ህዝቡ ያተረፈው ተጨማሪ ግብር ነው።

አቤ ወታደራዊውን መንግሥት መተንበይ የቻለው የሀገሪቱንም ሆነ የአለምን ተጨባጭ ሁኔታ በመገንዘቡ ነው። በሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ የኃይለሥላሴን መንግሥት ለመገልበጥ የተለያዩ ሙከራዎች የተደረጉ ሲሆን በ1953 ግን ከሞላ ጎደል የተሻለ ሙከራ ተደርጎ ነበር። ይህን መፈንቅለ መንግሥት አቤ ጠንቅቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ደጋፊም እንደነበር በመንግሥት ይጠረጠር ነበር። ልቦለዱም የታተመው መፈንቅለ መንግሥቱ ከተካሄደ ከሁለት አመት በሁዋላ በመሆኑም መነሻ አድርጎታል ብሎ በድፍረት መግለጽ ይቻላል። የአለምን ተጨባጭ ሁኔታንም ስናይ ስልጣናቸውን በሰላማዊ ምርጫ ለህዝብ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ያልሆኑ መንግሥታት የመጨረሻ እጣቸው በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት መውረድ ብቻ ሳይሆን የሚገጥማቸው ሞት፣ ውርደትና እንግልት ነበር። በመፈንቅለ መንግሥት ስልጣን የሚይዙ ወታደራዊ መንግሥታትም የህዝቡን የለውጥ ፍላጎት አኮላሽተው ሀገራትን ለከፋ ችግር ማጋለጣቸው በተለያዩ ሀገሮች የታየ ክስተት ነው። ስለዚህ አቤ *አልወለድምን* ሲጽፍ የአለምም ሆነ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎች መነሻዎቹ ነበሩ ማለት ይቻላል። ነቢይ ያሰኙትም በእነዚህ ምክንያት ድርሰቱ ተጨባጭ ሆኖ መገኘቱ ነው። ኤልያስ (1991፣ገጽ 12) ይህን ሁኔታ አስመልክቶ ሲገልጽ ያለው እንደሚከተለው ነበር፡-

> አልወለድም የወታደራዊ አገዛዝን እኩይነት ግልጥልጥ አድርጎ ያሳያል። ኢትዮጵያ ወደዚህ አይነቱ ሥርዓት ልትገባ ትችላለች የሚል ጭንቀትና ሥጋት ነበረው፤ አቤ ሲመክራቸውና ሲወቅራቸው የኖሩት የአገሪቱ መሪዎች ለዚህ ዓይነቱ አስከፊ ሥርዓት አሳልፈው ሰጧት።

አቤ ጉብኛ *አልወለድምን* በ1966ቱ አብዮት ወቅት ዳግም የማሳተም እድል ቢያገኝም በልቦለዱ የተገለጸው እውነት ደርጉንም እንደሚመለከት በመረዳታቸውና ከለውጡ በኋላ ባሳተማቸውም *ፖለቲካና ፖለቲከኞች* በመሳሰሉት ድርሰቶቹ እንደተቻቸው በመገንዘባቸው ወቅሰውታል፣ አዲስ አበባን

ለቆ ወደትውልድ አካባቢው ተመልሶ እንዲኖርም አስገድደውታል፡፡ አሟሟቱንም አስመልክቶ ቢሆን የደርግ መንግሥት እጅ እንዳለበት የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው (ኤልያስ፣ 1991)፡፡

## *የአልወለድም* ውክልና ስልት

አንድ እውነት በልቦለድ ውስጥ በተለያየ ስልት መገለጽ ይችላል፡፡ በገሀድ ወይም በስውር፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ በዝርዝር ወይም በአጭሩ፡፡ እውነቱ በሽፋን የሚገለጽ ከሆነ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ይቻላል - በምጸት፣ በጥቁምታ፣ በማጋነን፣ በተምሳሌት፡፡ አቤ በ*አልወለድም* ከላይ የተጠቀሱትን እውነቶች የገለጸው በተለያየ ስልት ነበር፡፡ አንዱ ስልት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ በመጠቀም ነበር፡፡ የልቦለዱ ዋና መቼት ኢይዝራኤሎስ ፈጠራ ይሁን እንጂ መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢይዝራኤል ከሚለው የእስራኤል ከተማና ከሆሴዕ ታላቅ ልጅ ስያሜ የተወሰደ ነው፡፡ ለዚህ ፍንጭ የሚሰጠው ደግሞ በመሬት ጉዳይ ከአቀንቃኙ ገጸባህሪና ከፊዩዳሉ ገዥ ሙሴ ገራቢዶስ ጋር ፣ንጉሥ አክአብና ባለቤቱ ኤልዛቤል የወይን እርሻውን ከነጠቁት ናቡቴ ጋር ተያይዘው መጠቀሳቸው ነው፡፡ እንደ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት* (1992) አፈታት ኢይዝራኤል የሚለው ስም እግዚአብሄር የኢዩን ነፍሰ ገዳይነት ‹‹የኢይዝራኤልን ደም›› በዘሮቹ ላይ እንደሚበቀል የሚያመለክት ስም ነበር (ሆሴዕ 1፣4፡5)፡፡ በሀገርም ብንወስደው ኢይዝራኤል የቦታ ስም ሲሆን የንጉሥ አክአብና የኤልዛቤል ግዛት ነበር፡፡ ሆኖም ንጉሥ አክአብና ሚስቱ ኤልዛቤል በናቡቴና መሰሎቹ የማይገባቸውን በመፈጸማቸው፣ በሥልጣናቸው በመባለጋቸው እግዚአብሄር አምላክ ኢዩን ያስነሳባቸዋል፡፡ ኢዩም በአክአብ ላይ እግዚአብሄር እንዲደርስ የፈቀደውን በመፈጸሙ አራት ዘሩ እንዲገዛ ፈቃዱ የነበረ ቢሆንም ከተፈቀደለት በማለፉ፣ የእግዚአብሄርን ህግ ከልቡ ባለመጠበቁና የንጹሃንን ደም በማፍሰሱ መጨረሻው ውድቀት ሆነ (*መጽሐፈ ነገሥት* 10፡30 - 35፣ ትንቢተ ሆሴዕ 1፡ 4 - 5)፡፡

በመጽሐፉ ዐውድ የንጉሥ አክአብና የንግሥት ኤልዛቤል አገዛዝ ለኃይለሥላሴ አገዛዝ ምሳሌ የሚሆነው ንጉሣዊ በመሆኑ ብቻ አይደለም፡፡ አክአብ ክፉ ግብሩን ደፍረው የሚተቹትን ነቢያቱን እንደሚገድልና እንደሚያንገላታ ሁሉ ኃይለሥላሴም ሥልጣናቸውን ተቀናቃኞች ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ያጠፏቸው፣ያስሯቸው ያሳድዷቸው ነበር፡፡ አክአብ የደሆችን መሬት እንደነጠቀው ሁሉ ኃይለሥላሴም በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ ገበሬውን ከመሬቱ እያፈናቀሉ[5] ለራሳቸውና ለመሳፍንቱ ለታማኝ አርበኞቻቸው አከፋፍለዋል፡፡ በመጽሐፈ ነገሥት 1 በቁጥር 21፤ 1 - 28 እንደተገለጸው

[5] በአሸኔ ጌታቸው ፍልሚያ (2001) ረጅም ልቦለድ ከናቡቴ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በአርሲ ክፍለ ሀገር ጥዱ የተባለ አርበኛና ታታሪ ገበሬ ያለማውን መሬት የወረዳው አስተዳዳሪ ከጥዱ እርስት አጠገብ መሬት ለነበረው ለበላይ ገኘው መተያያ ይሆን ዘንድ ነጥቆ ከእርስቱ ሲቀላቀል እናነባለን፡፡ ይህን መሰል የመሬት ወረራና የሀገሬው እንግልት በታሪክ መጽሀፎችም (ባህሩ፣ 2002) ተመዝግቦ የሚገኝ ነው፡፡

ንጉሥ አክአብ ከቤተመንግስቱ አቅራቢያ የወይን እርሻ የነበረውን የናቡቴን መሬት በሽያጭና በለውጥ ለማግኘት ሞክሮ ሳይሳካለት ሲቀር ንግሥቲቷ ኤልዛቤል ናቡቴን በሰዎቿ አስገድላ መሬቱን ወስደዋል፡፡ በዚህ ድርጊታቸው እግዚአብሔር አምላክ በመቆጣቱ አክአብ ከናቡቴ የነጠቀውን መሬት ሊጎበኝ ወደስፍራው በወረደበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስን ልኮ ሰውዬውን እንዳስገደለው ርስቱን ሊወስድ በማሰቡ ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ቦታ የሱንም ደም እንደሚልሱት ነግሮታል፡፡ እንዳለውም ሆኗል፡፡ ዳግመኛም እግዚአብሔር አምላክ ኢዩን አስነስቶ ኤልዛቤልንና ዘሮቿን አጥፍቷል (መጽሐፈ ነገስት 1፤ 17 - 28)

ከላይ ባሉት አንቀጾች እንደተገለጸው የንጉሥ አክአብና የናቡቴ ጉዳይ በልቦለዱ በአንድምታ ብቻ ሳይሆን በገሀድ የልቦለዱ ታሪክ ማንጸሪያ ሆኖ ቀርቧል፡፡ አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ከሚሠራበት ድርጅት ሠራተኞችን ለአመጽ አነሳስቷል ተብሎ ከተባረረ በኋላ ከጥቂት ሰዎች ጋር ዱር መንጥሮ ማልማት የጀመረው ስፍራ ለምቶ ሺዎች እየተዳደሩበት ሳለ ከገዥዎቹ ወገን ሙሴ ገራቢዶስ የተባለ ባላባት ያባቴን መሬት ነው ያለማችሁትና መሬቱን ልትለቁልኝ ይገባል ሲል ክስ ባቀረበባቸው ሰዓት አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ፡-

> *የራሴና የጓደኞቼ ላብና ደም ተንጠፍጥፎ ያለመለመውን ገነት በጊዜና በሥልጣን የተመካ ትዕቢተኛ ልንጠቅህ ሲለኝ ዝም ብዬ የማይ ይመስላችኋል? እኔና ጓደኞቼ እንደሌሎች ገበሬዎች ሁሉ አሻንጉሊቶች ሁነን የምንገኝ ይመስላችኋል? የዓለምን ሁኔታና የሰው ልጆች በአካላዊና በመንፈሳዊ ሥልጣኔ የደረሱበትን ደረጃ አጣርቶ የሚያውቅ ሰብአዊ ክብሩንና ነጻነቱን ከሕይወቱ በላይ የሚወድ ፍጡር በማንኛውም ዓይነት ትዕቢት ለተወጠረ ዕቡይ የማይንበረከክ መሆኑን አታውቁም? የመጽሐፍ ቅዱስ አክአብ ናቡቴን ገድሎ የአትክልቱን ቦታ እንደወረሰ ንጉሥ ዳዊትም ኦርዮንን ገድሎ ሚስቱን እንደወረሰ በፊት እኛን ገድላችሁ ዓይናችሁ የቀላበትን ለም ምድር ዝረፉ እንጂ በሕይወት እያለንስ አይቻልም… (አልወለድም፣ ገጽ 130-131)*

በማለት አክአብንና ናቡቴን በገሀድ ይጠቅሳል፡፡ ይህ ገሀድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ ከላይ ስንገልጽ እንደነበረው ኢይዝራኤሎስ፣ ኢይዝራኤል ከሚለው ከመጽሐፍ ቅዱስ፤ ከአክአብ ግዛት ስያሜና መጠሪያ የተወሰደ ነው፤ ታሪኩም በተዘዋዋሪ በመጽሐፍ ቅዱሱ የአክአብና ኢዩ ታሪክ ጋር የተመሳጠረ ነው ብንል ስህተት አይሆንም፡፡

ኢዩ በልቦለዱ ዐውድ መፈንቅለ መንግሥት አድራጊውን የማርሻል ጃፌሮስን መንግሥት፣ በገሀዱ አለም ደግሞ ደርግን ይወክላል፡፡ በልቦለዱ ወታደራዊው መንግሥት የቀድሞውን ሥርዓት ገዥዎች ካወረደ በኋላ በሞት ነው የቀጣቸው፡፡ በሞት ከተቀጡት ሰዎች ዝርዝር ውስጥ በልቦለዱ ታሪክ መሬቱ የአባቴ ርስት ነውና ይገባኛል ሲል በአቀንቃኙ ገጸ ባህሪ በአክአብ ተመስሎ

የቀረበው ሙሴ ገራቢዶስ አንደኛው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የ1966ቱን አብዮትና በሞት የተቀጡትን 60 የመንግሥት ባለሥልጣናትና የንጉሣውያን ቤተሰቦች ሁኔታ ያስታውሰናል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ኢዩ ምንም እንኳን የአክአብን ሥልጣን እንዲወርስ እግዚአብሄር አምላክ ቢያስነሳውም የአክአብን ዘር ብቻ ሳይሆን እንዲገድል ያልተፈቀደለትን ነቢያትን ሁሉ ገድሏል፡፡ በዚህም እግዚአብሄር አምላክን አስቆጥቷል፡፡

ከዚሁ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ ሳንወጣ አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ አንዳንድ የእየሱስን መገለጫ ነጥቦች ይጋራል (ለድሆች መቆርቆር፣ ማስተማርና መስዋዕት አስከመሆን ድረስ ራስን አሳልፎ መስጠት፤ ከሞት በሁዋላ በመንፈስ መገለጽ፤ በእየሱስ ስልት መናገር፣ በቀጥታ አድማጩን ማናገር፣ ስለምናዊ ጥያቄ መጠየቅ፤ የአይሁድ ካህናት እየሱስን እንደካዱት አቀንቃኙም በሥርዓቱ አስፈጻሚዎች መገፋት)፡፡ ቀጥሎ ከእነዚህ ነጥቦች የተወሰኑትን በዝርዝር ለማየት ይሞከራል፡፡

እየሱስ የእግዚአብሄርን መንግሥት እንዳስተማረ አቀንቃኙም የነጻነትና ዲሞክራሲን መንገድ አስተምሯል፡፡ እየሱስ በአይሁዳውያን እንደተሳደደ አቀንቃኙም በኢይዝራኤሎስ ባለሥልጣናት ተሰዷል፡፡ እየሱስ በማስተማሩ እንደተከሰሰ ሁሉ አቀንቃኙም በትምህርቱና በሚከተለው አቋም ምክንያት ተከሷል፡፡ እየሱስ እንደተሰቀለ ሁሉ አቀንቃኙም በጥይት ተደብድቦ ተገድሏል፡፡ ከሞቱም በኂላ ተነስቶ በ*አልወለድም* ያነበብነውን ታሪኩን ጽፏል፡፡

አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ የእየሱስን መገለጫዎች የሚጋራ መሆኑን ያውቃል፤ እራሱንም የእየሱስ ደቀ መዝሙር (ወይም እየሱስን ምሳሌ አድርጎ የተነሳ) አድርጎ የሚቆጥር ይመስላል፡፡ ራሱን እውነትን ፈላጊና እኩይ ምግባርን የምጠየፍ ነኝ ብሎ ያስባል፡፡ በዚህም ምክንያት ሞትን በጸጋ እስከመቀበል ይደርሳል (*አልወለድም*፣ ገጽ 214 - 215 እና 219)፡፡ ይህንንም በተመለከተ በልቦለዱ እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

> እየሱስ ክርስቶስን ያህል ቸር መምህር የታመሙትን ስላዳነ ለተጎዱት ርኅራኄን ለተቸገሩት ቸርነትን ፍቅርንና ሰላምን ስላስተማረ በቅንዓተኞችና ምቀኞች ሴራ በመስቀል ተሠቃየ፡፡ እንደዚሁም ብዙ ሰዎች መልካም ስለሠሩ በራሳቸው ላይ ብዙ ችግርና መከራ እንዲሁም የሞት ቅጣት ደርሶባቸዋል፡፡
>
> ሌላው ቀርቶ ከሃይማኖትና ከፖለቲካ ጋር ያልተያያዙ የሥነ ፍጥረት ምሥጢሮችን በገለጹ ሊቆች ላይ ብዙ ሥቃይ ደርሷል፡፡
>
> እንግዲህ የመልካም ሰዎች ዕድል በክፉዎች መጠቃት ነው ማለት ነው፡፡

> መልካም የኔም ዕድል ከመልካሞቹ ሰዎች ዕድል ጋር ከተያያዘ ሞትን በደስታ መቀበል ያለብኝ መሆኑን ተገነዘብሁ።…(*አልወለድም፣ ገጽ* 214 -215)

> ሃይማኖት ያለኝ ሰው መሆኔን ከገለጽሁ አይቀር <u>የእየሱስ ክርስቶስ ተከታይ መሆኔን ልግለጸው</u>። እየሱስ የሰው ልጅም ቢሆን የእግዚአብሄር ልጅ በሁለቱም በኩል ቸር መሪ ነው። የሰው ልጅ በመሆኑ ለሰዎች ፍቅርን ርኅራኄን ቸርነትን ርዳታን በሥራና በማስተማር ገልጿል። ያምላክ ልጅ በመሆኑም ከፍተኛውና መልካሙ ትምህርቱ በጥቂት ሰዎች አስተማሪነት ለዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲደርስ አድርጓል። <u>እንግዲህ ሌሎችን የሃይማኖት መሪዎች እያከበርሁ እሱን ልከተለው። የኔም ክርስትያንነት በአንድ ወላዋይ ቄስ እጅ በውሃ ተጠምቄ፡- ክርስቶስ የሚጠላውን ሐሰትና ማጭበርበር እየሠራሁ ክርስቲያን ነኝ በማለት ሳይሆን እንደርሱ ቀን ትምህርትን ሳስተምር በግፈኞች እጅ ደሜ ፈስሶ በደሜ ተጠምቄ የክርስቲያንነትን ጸጋ በመቀበልና የክርስቶስን ምሳሌነት በመከተል ነው</u>። (*አልወለድም፣ ገጽ* 219፤ አጽንኦት የኔ)

አቀንቃኙ ገጸባህሪ እየሱስን እሚመስለው በግብሩ ብቻ ሳይሆን በአነጋገሩ ስልትም ነው። ስለምናዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፣ አድማጮቹን፣ ከሳሾቹን በሁለተኛ መደብ ፊት ለፊት ያናግራቸዋል፤ ድምጸቱም የእየሱስ ነው፤ የማስተማር፣ የመገሰጽ፣ የአዋቂነትና የትህትና ነው። ለምሳሌ እንዲሆነን ከመጽሐፍ ቅዱስና ከልቦለዱ ምሳሌዎችን እንይ፤ መጀመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንይ፡-

> ከእናንተ አንዱ ወዳጅ ቢኖረውና በእኩለ ሌሊት ወደ እርሱ ሄዶ “ወዳጄ ሆይ ሦስት እንጀራ አበድረኝ አንድ ባልንጀራዬ ከመንገድ መጥቶብኝ የማቀርብለት ምንም ነገር የለኝምና” ብሎ ለመነው እንበል።

> በቤት ውስጥ ያለውም “አታስቸግረን፤ በሩ ተቆልፏል፤ ልጆቼም አብረውኝ ተኝተዋል፤ ከእንግዲህ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም” ይለዋልን? እላችኋለሁ ወዳጁ በመሆኑ ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ ስለ ንዝነዛው ብቻ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል፤

> ስለዚህ እላችኋለሁ፤ ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፣ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ ምክንያቱም የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፣ የሚፈልግም ያገኛል፤ በር ለሚያንኳኳም ይከፈትለታል። ከእናንተ መካከል አባት ሆኖ ልጁ ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው ይኖራልን? ወይስ ዕንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት

ካወቃችሁበት የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ? (ሉቃስ 11፤ 5 - 13)

በጥቅሱ እየሱስ ሰዎቹን በሁለተኛ መደብ እናንተ እያለ ነው የተናገረው፤ በንግግሩ ወቅት ስለምናዊ ጥያቄዎችን ይጠይቅና ከነሱ መልስ ሳይፈልግ ራሱ መልስ ይሰጥ ነበር፤ በንግግሩ የበላይነት (የአምላክነት) ባህሪ ይታይበት ነበር፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝም ይገስጥ ነበር። ከዚሁ ጋር የሚሄድ ተጨማሪ ምሳሌ እንይ፤ ምሳሌው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው፤ እየሱስ ከእርሱ ጋር ምግብ እንዲበላ የጋበዘው ፈሪሳዊ እጁን እንዳልታጠበ ባየ ጊዜ መደነቁን አስተውሎ እንዲህ አለው፡-

አሁን እናንተ ፈሪሳውያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጫዊ ክፍል ታጸዳላችሁ፤ ውስጣችሁ ግን በስስትና በክፋት የተሞላ ነው። እናንት ሞኞች የውጭውን የፈጠረ የውስጡንም አልፈጠረምን? ነገር ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት አድርጋችሁ ስጡ፤ በዚህ ጊዜ ሁሉም ንጹህ ይሆንላችኋል።

እናንት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፤ ከአዝሙድና ከጤና አዳም እንዲሁም ከአትክልት ሁሉ ዐሥራት ታወጣላችሁ፤ ሆኖም ፍትሕንና እግዚአብሔርን መውደድ ቸል ትላላችሁ፤ ነገር ግን ያንን ሳትተዉ ይኸኛውን ማድረግ በተገባችሁ ነበር።

እናንት ፈሪሳውያን ወዮላችሁ በምኩራብ የክብር መቀመጫ፣ በገበያ መካከልም እጅ መነሣትን ትወዳላችሁና።

ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበትን የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ ወዮላችሁ።(ሉቃስ፣ 11፤ 39 - 45)።

እንደላይኛው ምሳሌ ሁሉ በዚህኛውም አስረጂ እየሱስ ስለምናዊ ጥያቄ ጠይቋል፤ ፊት ለፊት አናግሯቸዋል፤ ገስጿቸዋል። እንደ እየሱስ ሁሉ በልቦለዱ ውስጥ አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ፊት ለፊት ማናገር ብቻ ሳይሆን በድፍረት ይገስጻቸዋል፤ ምክር ይለግሳቸዋል። አስረጂ እንይ፡-

ስለፍቅር መልካምነት ታወራላችሁ። ፍቅርን የሚያነሳቁል ጠብ ትፈጥራላችሁ። የሕዝብን መብት ትገፋላችሁ፤ አዲሶቹ ገዥዎችም ያለፈውን ያገዛዝ ዓይነት ትነቅፋላችሁ። ከድሮው በበለጠ ከባድ አገዛዝ ህዝብን ታሰቃያላችሁ። ነገሥታትና መሳፍንት ይለብሱት የነበረውን በወርቅ የተንቆጠቆጠ ልብስ ትረግማላችሁ፤ እራሳችሁ ደረታችሁንና ትከሻችሁን እስኪከብዳችሁ ድረስ የወርቅ ጌጣጌጦችን ትሸከማላችሁ፤ ወዮላችሁ! ተራ ህዝብ ለሆናችሁ ወገኖቼ! በጡንቻውና ባበጠ ቦርሳው የሚመካ ሁሉ ለባርነት ለሚያጫችሁ ምስኪኖች ወዮ!

> እናንተ ህዝቦች እውነቱን ልንገራችሁ! ያለፈውን ለመንቀፍና ያለውን ለማመስገን ያገኛችሁትን ድል እንደ እድገት አትቁጠሩት፤ አዲሱ ጠቃሚ መስሏችሁ ሳትቀረጥሙ አትዋጡት። ሁሉንም መርምራችሁ እውነተኛ ዋጋውን ስጡ። (*አልወለድም*፣ *ገጽ* 226 - 227)

አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ተዓምር መስራቱም ከእየሱስ ጋር ያመሳስለዋል፤ ገና ከጽንሱ ጀምሮ ነው ተዓምር የሚያሰኝ ነገር የፈጸመው። አንደኛ ነገር ሳይወለድ በፊት ገና በእናቱ ማህጸን የደረሰ ጽንስ ሆኖ ሳለ አልወለድም ሲል እናቱን ያናግራታል። የሚያናግራት ግን ባላወቀው ኃይል ተሞልቶ ነው። የሚናገረውም ነገር የበሰለ ነው፤ እውነት በሌለበት ዓለም ለመኖር አልወለድም። ንግግሩ ቃል በቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

> አንድ ሰው በጥን ሲያልፍ ስለመድኃኔዓለም አለቺውና ሳንቲም ሲሰጣት ከጅዋ ላይ ከነበረው ሌላ ሳንቲም ጋር ተጋጭቶ ቅጭል ሲል በሆዷ ውስጥ ከተኛሁት እንቅልፍ ብንን አልሁ። ከእንቅልፍ መንቃት ብቻ አይደለም። ከድንቁርና ስሜትም ነቃሁ።
>
> ማ እንደሆነ ያላወቅሁት ኃይል ምቾትና ነጻነት ወደሌለበት ዓለም የምሄድ መሆኔን እንዳውቅ አደረገኝ። ስንት ስፋትና መጠን ያላት ዓለም አሁን ከምገኝበት ጠባብ ሆድ እጅግ የምታንስ መሆኗን አሳወቀኝ። ሙሉ ነጻነቴን እንደያዝሁ ባለሁበት የናቴ ሆድ ውስጥ ፍርግጥግጥ አልሁ። ሆዷንም በርግጫ ደበደብሁት።
>
> "አዬ ፍዳዬ እዚሁ ላይ ደረሰብኝ መሰል! ነገሩማ ወዴት ልደርስ ኑሯል?" አለች በቀላሉ የምወለድ መስሏት።
>
> "በጭራሽ አልወለድም" አልሁ፤ በጩኸት። እሷም ሆዷ እንደተለመደው ጩርር ያለ መስሏት ነበር እንጂ እንደዚህ ያለ በሰው ታሪክ ውስጥ እንግዳ የሆነ ነገር ይሆናል ብላ አልተጠራጠረችም፤ በሆዷ ውስጥ ሁኖ የሚናገር ሕጻን? ማን ሊጠረጥር ይችላል? ለኔም ለራሴ ማመን ያስቸግረኛል።
>
> ደኅና ቦታ ልያዝ መሰል አለች ከመንገዱ ወዳለው የካብ አጥር ስር ጠጋ እያለች "በፍጹም አልወለድም" አልሁ አሁንም ጮኽ ብዬ፤ ነገሩ ግራ ሆነባት ወዲያና ወዲህ ፊቷን እያዞረች ሰው እንዳለ ማየት ጀመረች። ከዚያም ቀጥላ "ወይ ግሩም! ሰይጣን ጠራኝ ልበል?" አለች።
>
> "አዬ! ደግሞ ሰይጣን? እኔ ነኝ። አልወለድም" አልኳት። ወደሆዷ አንገቷን ዝቅ አደረገችና "አንተ ማን?" አለች፤ በታላቅ ፍርሃትና ጭንቅ። እንግዳው ነገር የተሠራው በሆዷ ውስጥ ሆነና የምታመልጥበት ዘዴ ባይኖራት እንጂ በዚህ ጊዜ ልቧ እስኪፈርስ ብትሮጥ በወደደች። (*አልወለድም*፣ *ገጽ* 41 - 42)

በተመሳሳይ በማዋለጃ ክፍል ውስጥ በቀዶ ጥገና ያዋለደውን ሃኪም “ቆይ ግድ የለም አንተ ደደብ መኖርን እንጂ ለመኖር የሚያስፈልገውን የማታውቅ ሟቹን አካል የምትጠብቅ የማይሞተውን መንፈስ ግን የማታውቅ በዚች ቀን አንተ አዋቂ ሐኪም ተባልህባት እኔ ግን ወደማልፈልጋት መከራና ሥቃይ አዘጋጅታ ወደምትጠብቀኝ ዓለም መጣሁባት፡፡ ዕውቀትህን አደንቃለሁ፡፡ ሰውን በማገልገልህና ጊዚያዊ ሥቃይን በመካላከልህ አመሰግንኻለሁ፡፡” ሲለው ሃኪሙ ደንግጦ ሲወድቅ እናነባለን (*አልወለድም*፣ ገጽ 52 - 53)፡፡ በህጻንነቱ ወራትም ክርስትና ሊነሳ ሊጠመቅ ሳለ “ምነው አባቴ በጠዋቱ በቀዝቃዛ ውሀ ያደፍቁኛል” ሲላቸው ቄሱ ሲደነግጡ እናነባለን (*አልወለድም*፣ ገጽ 64 - 65)፡፡ ይህ ሁሉ እንግዲህ ህጻኑ በልዩ መንፈስ ተሞልቶ የሚሰራው ተዓምር ነው፡፡ ተዓምርነቱንም ራሱ ስለሚገነዘበው በምዕራፍ አንድ “ከናቴ ሆድ ጀምሮ የሠራሁትን እንግዳ ሥራ ስታዩ አንድ በሰው ሕይወት ላይ የተፈጸመ ተአምር ታያላችሁ፡፡ በክፋት መንገድ ስትተረጉሙት፣‘ይህ ሰው የዲያቢሎስ ዲቃላ ነው፤” ብላችሁ ለማመን፣ በደግ ስትተረጉሙት ግን እግዚአብሄር በነጻነት ክብሪት ለኩሶ የፈጠረው ሕይወቱን እያቃጠለ ለሰው ልጆች የነጻነት ጧፍ ነው› ብላችሁ ለማመን እንደምትገደዱ አምናለሁ፡፡” (*አልወለድም*፣ ገጽ 36) ሲል መግለጫ ይሰጣል፡፡

ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ ጋር ተያይዞ የአቀንቃኙን ገጸ ባህሪ ሁኔታ ስናስብ በቅዱሳን ታሪኮች (እንደ ተክለኃይማኖት፣ ገብረመንፈስ ቅዱስ..) እንደምናነበው ከናቱ ሆድ ጀምሮ የተመረጠ ነው ብለን ልናስብ እንችላለን፡፡ ይህ እንዴት ይሆናል ብለን ጥያቄ እንዳናነሳ አስቀድሞ መከላከያ ያዘጋጃል፡፡ ለምሳሌ እንዴት ጽንስ ይናገራል እንዳንል በልዩ መንፈስ መሞላቱን ቀድሞ ነግሮናል፡፡ ይህ በልቦድ አጻጻፍ ‹‹ኒዩትራላይዜሽን›› የምንለው ቴክኒክ ነው፡፡ የልቦዱ ታሪክ ተጋነነ ብለን ብናስብም እንኳን መከላከያ አበጅቷል፤ ባያበጅም በፖለቲካዊ ልቦለድ አጻጻፍ ዘልማድ ግነት የተለመደ አሰራር ነው (Hawthorn፣ገጽ 1992)፡፡

ከእየሱስ ጋር የሚያመሳስለው ሁለተኛው ተዓምራዊ ክንዋኔ ታሪኩን የጻፈው የሞት ፍርድ ተፈርዶበት በጥይት ተደብድቦ ከሞተ በኋላ በመንፈስ መጥቶ ነው (*አልወለድም*፣ ገጽ 236)፡፡ ይህም በልቦለዱ የመጨረሻ ገጽ የመጨረሻ አንቀጽ ‹‹...ይህን <u>ለመጻፍ የቻልሁትም በመንፈስ መጥቼ</u> ነው›› ከሚለው ከአቀንቃኙ ገጸባህሪ አንደበት መረዳት እንችላለን (አፅንኦት የእኔ)፡፡ ይህን ውክልና አስፍተን ስናየው ደግሞ ደራሲውም ቢሆን ከአቀንቃኙም ሆነ ከክርስቶስ የሚጋራው ነገር አለ፡፡ ከአቀንቃኙ መምህርነትን፣ ድፍረትን፣ ለውጥ መሻትን፣የህዝብ አፈቀላጤነትን፣ መስዋዕትነትን ይጋራል፡፡ የእውነት ጠበቃነትንና ለእውነት መሰዋትን አስመልክቶ ደግሞ ክርስቶስን ምሳሌው እንዳደረገ ከህይወት ገጠመኙ መረዳት እንችላለን፡፡ ከእረፍቱ በኋላ በድርሰቶቹና በገጠመኞቹ መወያየታችንም ቢያንስ በመንፈስ ከእኛ አለመለየቱን ያሳስበናል፡፡

የአጻጻፍ ቴክኒክ ከተነሳ *አልወለድም* ከመሬት ከበርቴው ገጸ ባህሪ ሙሴ ገራቢዶስና ከወታደራዊው መሪ ማርሻል ጃቬሮስ በስተቀር በስም የተጠቀሱ ገጸ

ባህሪያት የሉም። አቀንቃኙ ገጸ ባህሪ፣ እናቱ፣ ዶክተሩ፣ ቄሱ ሁሉ ስም የለሾች ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያት ስም ባለመጥራት ከሳንሱር ለማለፍ ብቻ ሳይሆን ስም ያላቸው ገዥዎች/መሪዎች መሆናቸውንና ድሀው/ሠራተኛው ክፍል ግን ስም የለሽ መሆኑን ለማሳየት ነው። *አልወለድም* እነዚህን በመሳሰሉ አጻጻፍ ስልቶቹ (ፍቅሬ 'ፋንታስቲክ' ሊትሬቸር ቢለውም) - በአጻጻፍ ስልት ማፈንገጡ፣ያልተለመደ መቼት መያዙ፣ የተጋነኑ ስም የለሽ ገጸ ባህሪያት መሳሉ፣ ተአምራታዊ ክንዋኔዎች መጠቀሙ፣ በይነ አሀዳዊ ስልት መከተሉ (ከመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሱ) በከፊልም ቢሆን የዘመናዊነትንና ድህረ ዘመናዊነት ባህሪን ይጋራል።

### ማጠቃለያ

ከላይ በትንተናው መረዳት እንደተቻለው አቤ *አልወለድም* ማንንም የማይመለከት የልቦለድ ፈጠራ ነው ይበል እንጂ በልቦለዱ የገለጸው እውነት የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ነው። የወከለው የኃይለሥላሴንና የደርግን ሥርዓት ፖለቲካ ነው። አልወለድም መጀመሪያ የታተመው በ1955 ሲሆን የኃይለሥላሴን ሥርዓት መወከሉ ብዙ ላያስደንቅ ይችል ይሆናል። የሚያስደንቀው ግን 11 ዓመት ቀድሞ የደርግን ሥርዓት መወከሉ ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ይህ የሆነበት ምክንያት ደራሲው የሀገሪቱንም ሆነ የአለምን ተጨባጭ ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገንዘቡና ድርሰቱን ከመጻፉ ሁለት አመት ቀደም ብሎ ተሞክሮ የነበረው የ1953 መፈንቅለ መንግሥት መነሻ ስለሆነው ነው። ሥልጣንን ሙጥኝ ብለው የያዙ አፋኝ መንግሥታት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል አስተምሯል። ጋዜጠኛ ነበርና በየወቅቱ በውጭ መገናኛ ብዙኃን የሚሰማቸው የመፈንቀለ መንግሥት ዘገባዎችም ግንዛቤውን አስፍተውለታል። የ1953 መፈንቅለ መንግሥት በፖለቲካ ሳይንቲስቱ ገርማሜ ይጠንሰስ እንጂ ግብሩን ፈጻሚዎቹ የጦር መኮንኖች ነበሩ (ባህሩ፣2002)።

ከአጻጻፍ ስልት ረገድ አቤ በተለይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቁምታ እንዲጠቀም የረዳው የቤተ ክህነት ትምህርቱ ነው። በዚህ ምክንያት ነው ኢትዮጵያን በኢይዝራኤል፣ ኃይለሥላሴን በአክአብ ደርጉን በኢዩ፣ አቀንቃኝ ገጻባህሪውን በክርስቶስ የመሰለው።

በትንተናው የመጨረሻ ክፍል እንደተገለጸውም ለህዝብ መብት ተሟጋችነቱ፣ ለእውነት ጠበቃነቱ፣ ደፋርነቱ፣መብቱን ለማስከበር ዘወትር የሚማስን መሆኑ፣ አስተማሪነቱ፣ በጥቅም አለመደለሉና መስዋዕት መሆኑ አቤን በአቀንቃኙ ገጸ ባህሪ ህይወት ውስጥ እንድናየው ያስገድደናል። የእውነት መምህርነት፣ የለውጥ ፈላጊነትንና መስዋዕትነትን አስመልክቶ አቀንቃኙን ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን ምሳሌ ያደረገ ይመስላል።

በመጨረሻም ከትንተናው መረዳት እንደሚቻለው አቤ የድርሰት ጥማቱን ለመወጣት፣ ለገንዘብ፣ ለዝና ሲል የሚጽፍ ሰው አልነበረም። ይልቁንም

የህዝብና የሀገር ጉዳይ እያንገበገበው የሚጽፍ፣ ሀገሩንና ህዝቡን ተለውጦ ማየት የሚናፍቅ ደራሲ ነበር ማለት ይቻላል። ለዚህ ነበር አቤ በ*አልወለድም* የሥርዓቱን ችግር ያሳየው፣ ችግር ማሳየት ብቻ ሳይሆን ስጋቱንም የገለጸው፤ ስጋቱን ለማስወገድ ደግሞ መፍትሄ ነው ብሎ የገመተውን ነገር የጠቆመው። ህዝብንም ችግሩን በማሳየትና ለመብቱ እንዲሟገት ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና ነበር የተጫወተው። በዚህም በሀዲስ ታሪካውያን አስተሳሰብ ሥነጽሑፍ በሚጻፍበት ዘመን ፖለቲካዊ ማህበራዊና ባህላዊ ዐውድ እንደሚቀረጽ ሁሉ ፖለቲካውን፣ ባህሉን በመቅረጽ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል የሚለውን አስተሳሰብ ተጨባጭነት ማረጋገጥ ይቻላል።

## ዋቢ መጽሀፍት


ሀዲስ ዓለማየሁ (1982) *ፍቅር እስከ መቃብር* (7ኛ እትም)። አዲስ አበባ። ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

መስፍን ማሞ (ቀን የለውም)። *አልወለድም፡ አስተያየት*: Retrieved from Ethiopiazare.files.wordpress.

በሪሁን ከበደ (1992)። *የኃይለሥላሴ ታሪክ*፡ አዲስ አበባ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አሸኔ ጌታቸው (2001) ፍልሚያ። አዳማ። እድር ማተሚያ ቤት።

አቤ ጉበኛ (1993)። *አልወለድም* (2ኛ እትም)። አዲስ አበባ። ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ኤልያስ አያልነህ (1991)። *የአቤ ጉበኛ ብዕራዊ ተጋድሎ*፡ አዲስ አበባ። ብራና ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማበህበር (1992)። *የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት* (6ኛ እትም)።አዲስ አበባ። ባናዊ ማተሚያ ቤት።

Bahru Zewde (2002). *A History of Modern Ethiopia: 1855-1991* (2nd ed.). Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Bertens, H. (2001). *Literary Theory: The Basics*. London: Routledge.

Doğan, E. (2005). New Historicism and Renaissance Culture. *Ankara Üniversitesi Dilve Tarih-Coğrafya Fakültesi Dergisi*, 45(1), 77-95. Retrieved from www19.homepage.villanova.edu/silvia.nagyzekmi/teoria2010/

Fikre Tollossa (1983). *Realism and Amharic Literature* (1908 -1981). Disserttion, der Universitat Breman, Beman.

Ghirmai Negash (1995). Literature and Politics in Ethiopia: A case Study of Abe Gubenya's Alwellwdim. In Tadesse Adera and Ali Jemale (eds.) *Silence is not Golden:a Critical Anthology of Ethiopian Literature* (pp. 135-153) Lawrenceville: The Red Sea Press Inc.

Hawthorn, J. (1992). *Studying the Novel: An Introduction*. London: Hadder Arnold.

Holub, R. (1992). New Historicism and the New World Order: The Politics of Textuality and Power in German Studies. *Monatshefte*, 84(2), 171-182.

Kane, T. L. (1975). *Ethiopian Literature in Amharic*. Germany: Otto Harrassowizt.

Molvaer, R. K (1997). *The Creative Lives of Modern Ethiopia's literary Giants and Pioneers*. Asmara: The Red Sea Press, Inc.

Tesfaye Dagnew (1986) "*The Portrayal of Society and the Concept of Modernization in Abbe Gobegna's Novels*" MA Thesis, Addis Ababa University.

Tyson, L.(2006). *Critical Theory Today: A User-Friendly Guide*. 2nd ed. U.S.A: Routledge, Taylor and Francis Group.

Zekiye, ER (n.d.).Tom Stoppard's Arcadia: A Postmodernist/ New historicist Reading of the Play. Retrieved from http://Dargiler.ankara.edu.tr/Dargiler/13/190/1469.pdf.